# ከዓይን ያውጣህ በሉት!

ከዓሣዬ

10/20/10

ግሱን ገሥ፣ዘርፋን ዘርፎ
የደብተራውን ቅኔ ተቃኝቶ
የአያት የቅድመ አያቱን
ጋሻና ጦሩን አንሥቶ
ግርማ ሞገሱን ተላብሶ
በታጋይ ሰማዕታት፣ዕግር ተተክቶ
አገሩን ነጻ ሊያወጣ፣ከወያኔ ጉርንቦ ተናንቆ፣
እነሆ ባባቱ ራዕይ፣ባዲሥ ጉልበት
ይኸው ተነሣ ኢ.ወክንድ፣በጠላቱ ላይ ሊዘምት
እናም እንትፍ ትፍ ትፍ
ዕደግ ተመንደግ ብላችሁ መርቁት
ትግልህ ይሥመር፣ከዓይን ያውጣህ በሉት! ።

የጭቆና መረቡን በጣጥሣችሁ
እሥቲ ሞክሩኝ ባይ፣ዘረኛን አዋርዳችሁ፣
በታማኝ ተቃዋሚ
የተሰበረውን የሕዝብ ወኔ ጠግናችሁ
እንደ ጎህ ጬራ፣ብሩህ ተሥፋው ሆናችሁ፣
አዲስ አበባን በ38ኛው፣የልደት ዋዜማ
እንዳሸበረቃችኋት፣በኢ.ሕአፓ ወክንድ ዓርማ
አዎ! እኛም በጣም ኮራንባችሁ!
የክተት አዋጃችሁን፣ሥናይና ሥንሰማ! ።

በአዲስ መንበረ ሥልጣኑ ገና ሣይደሰት
ደርሦ ያልጠበቀው በድንገት
ሲያሥደነብረው በድንጋጤ፣እያስጓራው በጭንቀት
የስለላ ተቋሙ
የኢ.ሕአፓ ዴሥክ፣ዓይኑ ፈጦ ግራ ገብቶት
ላይምረው የተነሣው፣እየተከተለ ከገባበት
ለጣዕረ ሞቱ ሥቃይ፣ኢ.ወክንድ ታክሎበት
በዘረኛው ላይ፣
ሠይፋን መዞ መቅሰፍቱን ሊያወርድበት ፣
መጣሁ ብሎ
አሻራውን በመናገሻው አኖረበት ።
ታድያ እኛም ደሥ ብሎን መረቅናቸው
ጉልበታችሁ ይጠንክር
ትግሉም ይፋፋም አልናቸው! ።

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.